በድብቅ በብላቴ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ሲሰለጥኑ የነበሩ ምልምል ፖሊሶች ጊዜያቸውን ሳይጨርሱ በድንገት እንዲመረቁ ተደረገ፣

ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኖች ስለስልጠናው ምንም እንደማያውቁ ተገለፀ፣

በማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ ሁለት ከፍተኛ የሕወሓት ሹሞች እርስ በእርስ እየተናቆሩ መሆኑ ተጋለጠ፣

ሕወሓቶች በስልጣን ላይ ከፍተኛ ሽኩቻ ጀመሩ፣

የወያኔ ደህንነት በሁለት የተከፈለ መሆኑ ታወቀ፣ የሁሉቱም ቡድን ኃላፊዎች ለመለስ ተጠሪ ናቸው፣

በአዲስ አበባ የታክሲ ተራ አስከባሪ የሆኑ ወጣቶች ለደህንነት ስራ ተመልምለው ስራ ጀመሩ፣

የወያኔው ቀንደኛ ካድሬ ተስፋዬ መንገሻ አሁንም የምርጫ ቦርድ ዋና ፀኃፊ ሆኖ ተሾመ፣

ለምርጫው የወያኔ ካድሬዎች ውሰጥ ውስጡን እየሰሩ መሆኑ ታወቀ፣

የወያኔ ቡድን በልመና ስራ ላይ ያሉትን እናቋቁማለን ብሎ ከሕዝብ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለጦሩ ቀለብ መግዣ አደረገው፣

የኩባ ምክትል ፕሬዝዳንት ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ምክንያት ተጋለጠ፣

እነ ዳንኤል በቀለና ነፃነት ደምሴ ነገ ሊፈቱ ይችላል ተብሎ ተገምቷል፣

አባ ገብረ መድህን የ6 ሚሊዮን ብር መኪና ከየአድባራት በተሰበሰበ ገንዘብ ተገዝቶ ሊሸለሙ ነው የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል::

ወያኔ በድብቅ ሲያሰለጥን የነበረውን አንድ ብርጌድ የፖሊስ ሠራዊት ጊዜውን ሲያጠናቅቅ እንዲመረቅ መደረጉ ከፌዴራል ፖሊስ ምንጮቻችን የተገኘው ጥቆማ ገለፀ፡፡

ሳይታሰብ ድንገት የስልጠና ጊዜያቸውን ሳያጠናቅቁ እንዲመረቁ የተደረጉት እነዚሁ የፖሊስ ሠራዊት አባላት በብላቴ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ውስጥ ለጥቂት ወራት ያህል ሲሰለጥኑ ቆይተው እንደነበር የገለፁት ምንጮች በፌዴራሉ ፖሊስ አዛዥ የወያኔው ተላላኪ ወርቅነህ ገበየሁ ትዕዛዝ ድንገት እንዲመረቁ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል ብለዋል፡፡

የወያኔው ቡድን ዛሬ በሀገሪቱ ዙሪያ ከተጣቂ ኃይሎች ጋር በሚያደርገው ውጊያ የተነሳ በየከተማው ውስጥ አስፍሮት የነበረውን ጦር ወደ የግንባሩ በመውሰዱ መሀል ከተሞች ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ነፃ ወደ የግንባሩ መውሰዱ መሀል ከተሞች ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ነፃ መሆናቸው ያስደነገጠው የወያኔ ቡድን በተለያዩ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ውስጥ ምልምል ፖሊሶችን እያሰለጠነና እያስመረቀ ሲሆን በቅርቡ በለገዳዲ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ካምፕ ውስጥ ብቻ ከ3 ሺህ በላይ ፖሊሶችን አስመርቋል፡፡

አሁንም በተመሳሳይ ወታደራዊ ትምህርታቸውን ተከታትለው ያልጨረሱ ምልምል ፖሊሶችን ታህሳስ 15 ቀን በድንገት እንዲመቁ የተደረገ ሲሆን፣ ይህ በብላቴን የጦር ካምፕ ውስጥ ሲሰለጥኑ የነበሩትን ምልምሎች ከጥቂት የወያኔ ሹማምንት በስተቀር ማንም እንደማያውቅና እንዳልተገለፀላቸው ምንጮቹ ገልፀው በተለይም የሚመለከታቸው የፖሊስ አዛዦች ጭምር በድብቅ በብላቴ ካምፕ ውስጥ ሲሰለጥኑ የነበሩት ምልምሎች እንደማያውቋቸውና ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ጧት ወደ ስራ ገበታቸው ሲገቡ በአስቸኳዋይ ወደ ብላቴ የፖሊስ ምረቃ ሥነ ስርዓት ላይ እንዲገኙ ትዕዛዝ ሲሰጣቸው እንደተረገሙና በሚደረገው ነገር ሁሉ እንዳዘኑ ምንጮች አስረድተዋል፡፡

የሚመለከታቸው የፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖች አንዳችም ነገር ሳይገለፅላቸው ቆይቶ ስልጠናውን ሳያጠናቅቅ በሚመረቀው የፖሊስ ኃይል ሥነ ሥርዓት ላይ በድንገት እንዲገኙ ከወያኔው ተላላኪ ከወርቅነህ ገበየሁ ትዕዛዝ መሰጠቱ በእጅጉ አሳዛኝና የስራውን ተዋረድ የማያከብር ሥርዓት መሆኑን በመገንዘባቸው ሲበሳጩ እንደነበር ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በተለይም ወደ ምረቃ ሥነ ስርዓቱ እንዲሄዱ ሰኞ ዕለት በጧት ቢሯቸው እያሉ የተነገራቸው መኮንኖች ለምረቃው የሚያስፈልገውን ልብስ እንኳዋን ለማዘጋጀት ጊዜ አጥተው በለበሱት የወታደራዊ ልብስ በዚያው ወደ ብላቴ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ካምፕ የተጓዙ መሆኑን የምንጮቹ ዘገባ አስረድቷል፡፡

ዛሬ በግራና በቀኝ እንደ ብራና ተወጥሮ መላወሻ ያጡት የወያኔ ቡድን እና ሹማምንቱ ለስልጣን ሲሉ እርስ በእርሳቸው መሻኮት መጀመራቸውን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

እድሜው እያጠረ መሆኑን ያልተገነዘቡ በረሃ አመጣሽ የወያኔ ካድሬዎች ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ከሥልጣንና ገንዘብ በተጨማሪ ባላቸው የበላይነት ፈላጭ ቆራጭ ሆነው እራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውንም የሥልጣን ባለቤት እያደረጉ መሆኑን በቁጭት የሚገልፁት ምንጮቹ ሰሞኑንም በተመሳሳይ መልኩ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ውስጥ የተከሰተው ተጠቃሽ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

እነዚሁ ለማረሚያ ቤቱ መስሪያ ቤት ቅርበት ያላቸው ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ ሰሞኑን ሁለት የጀኔራል ማዕረግ ባላቸው ባለሥልጣናት መካከል የተነሳው ሽኩቻ የአስተዳደሩን መስሪያ ቤት ሠራተኞች በሁለት ጐራ የከፈለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ብርጋዴር ጄኔራል አብርሃም ወ/አረጋይ እና ብርጋዴር ጄኔራል አክሊሉ በተባሉ ግለሰቦች መካከል የኮሚሽነርነት ማዕረግ ይገባኛል እያሉ ሽኩቻ የጀመሩ ሲሆን፣ ሁለቱም ግለሰቦች የየራሳቸውን ደጋፊ ለማበራከት በሚያደርጉት ሩጫ የወህኒ ቤቱ አስተዳደር ለሁለት ተከፍሎ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽነር የነበረው መኮንን አሰጌ የተባለውን ግለሰብ ወዲ ሻምበል የተባለው የሕወሓት ሰው ስልጣኑን ሊረከብ አስቦ በተለያዩ ምክንያቶች ሲያዋክበው እንደነበር በኋላም መኮንን አሰጌ የተባለው ሰው በሕመም አሳብቦ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቅቆ የወጣ ቢሆንም ስራውን ከለቀቀ ከ6 ወር በላይ እንደሆነና እስከአሁን በእሱ ቦታ አንድም ሰው ያልተተካ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በዚህም ምክንያት የተነሳ ወዲ ሻምበል የተባለው ባለበት ቦታ እንዲቆይና ምንም አይነት የስልጣን ጥያቄ እንዳያነሳ የተነገረው ሲሆን ከሱ ስር ያሉት ሁለቱ የሕወሓት ጄኔራል መኮንኖች ባላቸው የስልጣን ጥም የተነሳ በተለይ አብርሃም ወ/አረጋይ የተባለው ግለሰብ በጥቅምት 1998 ዓ.ም በቃሊቲ ወህኒ ቤት ውስጥ ከ100 በላይ ዜጐች እንዲገደሉ ትዕዛዝ የሠጠና ያስጨፈጨፈ መሆኑ እየታወቀ ከተራ አዛዥነት ተነስቶ ዛሬ የብርጋዴየር ጄኔራልነት ማዕረግ የተሰጠው ሲሆን አሁንም ይሄ አይበቃኝም በሚል ለኮሚሽነርነት ቦታው እንዲሰጠው እየሯሯጠ ይገኛ ል ሲሉ ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

አክሊሉ የተባለው ግለሰብም ቢሆን በማረሚያ ቤት ውስጥ ያልሰራው በደል የሌለ ከመሆኑም ባሻገር በተለይም በወህኒ ቤት ፖሊሶች ላይ እየቀለደና እያሾፈ የሚኖር ግለሰብ መሆኑን አትተው ከወዲ ሻምበል ጋር በመሆን መኮንን ከስልጣን ለማባረር ሲያሴር የነበረ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ሁለቱ የሕወሓት ሹማምንቶች ገና ለገና ከበረሐ መጥተናል በሚል ለኮሚሽነርነት እርስ በእርስ እየተሻኮቱ ሲሆን በስሮቻቸው ባሉ ሠራተኞች ላይ ደጋፊ ለማግኘት በሚደረግ ግብ ግብ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች በሁለት ቡድን ተከፍለው እንደሚገኝ - ገልፀው ይህንን እየተመለከተ ለጊዜው ተጠሪ የሆነው ወዲ ሻምበል አንዳችም የማብረድ እንቅስቃሴ እንደማይታይበት ገልፀዋል፡፡

ወዲ ሻምበል በእናቱ ትግሬ በአባቱ ኦሮሞ በመሆኑ ደሙ ያልጠራና ብዙም ታማኝ ባለመሆኑ የኮሚሽነርነቱን ቦታ እንደማይሰጠው የተነገረው ሲሆን፣ ከእርሱ በታች ያሉት ሁለት የትግራይ ተወላጆችና የሕወሓት አባሎች ለመሾም እየተነታረኩ መሆኑንም ምንጮች አብራርተዋል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ወደ አሜሪካ የሚጓዘውን የሴቶች ልዑካን ቡድን እኔ ካልመራሁ አልሄድም በማለት የሥልጣን ጥያቄ ያነሳች ሲሆን፣ በአሁን ወቅት የሕወሓት ሰዎች ምን ሰምተው ነው እንዲህ ያለ ያፈጠጠና ያገጠጠ ጥያቄ ከማንሳትም አልፈው እርስ በእርስ ሊናቆሩ የበቁት ሲሉ የሚጠይቁ በርካታ ወገኖች ናቸው፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሥልጣኑን ለማጠናከር አስቦ በየጊዜው ከተለያዩ ማህበረሰቦች ጋር እየተገናኘ ውይይት እያደረገ ቢሆንም ያገኘው ውጤት የሌለ መሆኑን የሚጠቁሙት አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በዚህም ተስፋ ባለመቁረጥ አሁንም ተከታታይ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ሰሞኑን የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበርን ባነጋገረበት ወቅት የማህበራዊ ችግሩ በቅርቡ እንደሚቀረፍ ገልፆ በተለይ የኑሮ ውድነቱን ለመቅረፍ ስንዴ በርካሽ እየሰጠን ነው በማለት ለማታለል ያደረገው ገለፃ ፍፁም የሕፃን ጨዋታ መሆኑን የገለፁት እነዚሁ የፖለቲካ ተንታኞች «የስልጣን ባለቤት መሆን አለባችሁ» እያለም ለማታለል ጥረት እያደረገ መገኘቱ እራሱንና መሰሎቹን እያታለለ ካልሆነ በስተቀር ማንንም ሊሸውድ እንደማይችል ከወዲሁ ሊያውቁት ይገባል ሲሉም እነዚሁ ተንታኞች ገልፀዋል፡፡

አክለውም የወያኔው መሪ መለስ ሁሉን በእጁ ከማለቱም በተጨማሪ ለሚስቱ ያስታቀፋት ስልጣን ቀላል እንዳልሆነ ገልፀው ዛሬ ሕዝቡ የሚቀምሰው አጥቶ በችግር እየተወዛወዘ ባለበት ወቅት የሕወሓት ሰዎች ይህንን የመሰለ የስልጣን ሽኩቻ መፍጠራቸው ምክንያቱ ግልፅ አይደም ሲሉም አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በሌላ በኩል የወያኔው ቡድን ሀገሪቱን በሁለት የደህንነት መዋቅሮች ከፍሎ እየሰራ መሆኑን የደህንነት ቢሮ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

በሀገር ውስጥ ደህንነት ኃላፊ አቶ ጌታቸው አሰፋ መሪነት እየተንቀሳቀሰ ያለው የደህንነቱ ክፍል የሲቪል ደህንነትና የወታደራዊ ደህንነቱን በበላይነት እየመራ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊውን ጨምሮ እየተቆጣጠረ እንደሆነ አጋልጠዋል፡፡

የወታደራዊ ደህንነት ክፍል ኃላፊ ሜጀር ጄኔራል ዮሐንስ ገብረ መስቀል የተባለው የመለስ የአክስት ልጅ ሲሆን፣ በወታደራዊ ደህንነት ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ በጠቅላላ ለመለስ ዜናዊ ሪፖርት እንደሚያደርግ የገለፁት ምንጮች አሁን ደግሞ ለሀገር ውስጥ ደህንነት ተጠሪ ጌታቸው አሰፋ ሪፖርት እንዲያቀርብ መወሰኑ ታውቋል፡፡

በሕወሓቶች መካከል ሰሞኑን የተጀመረው የስልጣን ይገባኛል ክርክር በነዚህም በጌታቸው አሰፋና በሜጀር ጄኔራል ዮሐንስ ገብረ መስቀል መካከል እኔ አዛለሁ አንተ አታዝም በሚል ግጭት ተከስቶ እንደነበር ምንጮቹ ገልፀው አሁንም ለጊዜው ችግሩ የተቀረፈ ቢመስልም ጉዳዩ ስር የሰደደና በቀላሉ ሊነቀል የማይችል መሆኑ በግልፅ እየታየ ነው ሲሉም ገልፀዋል።

የሕወሓት ሹማምንቶች ምንም እንኳዋን በስልጣን ይገባኛል ሽኩቻ ቢያደርጉም ባላቸው የበላይነት ሕዝቡን አፍነው መተንፈሻ አሳጥተው ለመግዛት የሚያደርጉት ጥረት እንዲቀጥል እየሰሩ መሆኑን ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለመረዳት ተችሏል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባ ታክሲ ተራ አስከባሪነት እየሰሩ ያሉትን ወጣቶች ለደህንነት ስራ መልምለው በቀን አበል እየከፈሏቸው እያሰሯቸው መሆኑንም የደህንነት መሥሪያ ቤት ምንጮች አጋልጠዋል።

እንደነዚሁ ምንጮች ገለፃ በስውር ተራ በተራ ለአንድ ሳምንት ያህል በየቀበሌው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ የደህንነት ስልጠና ከሰጧቸው በኋላ ለጊዜው የሚከፈላቸው የገንዘብ መጠን ያልታወቀ በየቀኑ አበል እየተከፈላቸው የስለላ ስራ እንዲሰሩ መደረጉን ጨምረው ገልፀዋል።

በታክሲ ተራ አስከባሪነት አሁንም እየሰሩ በተጓዳኝ የደህንነት ስራ የሚሰሩት እነዚህ የከተማዋ ወጣት በተለይም ተፈላጊ ናቸው የተባሉትንና በሚሰሩበት አቅራቢያ ያሉ ሰዎችን ውሎ እና ከእነማን ጋር እንደሚገናኙ በየቀኑ ሪፖርት እንዲያደርጉ መደረጉንም ምንጮች ጨምረው አስረድተዋል።

የወያኔ ጉሰኛና ጠባብ ቡድን በለመደው መንገድ ሕዝቡን እርስ በእርስ አናክሶ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል የማያደርገው እና የማይፈፅመው ነገር የሌለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በቅርቡ በደቡብ ክልል ውስጥ በቀን ስራ ላይ የተሰማሩትን ወጣቶች በስለላ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ በቀን 50 ብር ውሎ አበል እየከፈለ የደህንነት ትምህርት የሰጠ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተመሳሳይ በአዲስ አበባም የታክሲ ተራ አስከባሪዎችን የደህንንት ስራ ትምህርት ተሰጥቷቸው በሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ምንጮች አጋልጠዋል።

በተለይም የማሚያ፣ የወረዳና የቀበሌ ምርጫ እየተቃረበ በመሆኑ በምርጫ ዙሪያ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ክትትል እንዲያደርጉ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ጥርጣሬ ውስጥ የሚወድቅ ካለ ለፖሊስ ነግረው በቁጥጥር ስር እስከማዋል ስልጣንም እንደተሰጣቸው ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

ሰሞኑን ደግሞ ምርጫ 97 በፈፀመው ወንጀል ሲወገዝ የነበረው ተስፋዬ መንገሻ የተባለው የወያኔ ምርጫ ቦርድ ምክትል ዋና ፀኃፊ የነበረው ግለሰብ ተመልሶ ባለበት ቦታ እንዲቀመጥ የወያኔ ጃሌዎች የተሰባሰቡበት የተወካዮች ምክር ቤት ተብየው አፅድቋል።

ሀገር አቀፍ ምርጫ ተደርጐ የወያኔ ሹማምንት በዝረራ ተሸንፈው የነበሩት በሙሉ ተስፋዬ መንገሻ እና መኮንን የተባሉት የወያኔ ቀንደኛ ካድሬዎች በማን አለብኝነት በገዛ ፈቃዳቸው በስልጣን ላይ እንዲቆዩ ያደረጓቸው በመሆኑ ለዚሁ ማካካሻ አሁንም ተስፋዬ መንገሻን ጨምሮ ሌሎች ሁለት ወያኔዎችም ምክትል ፀኃፊ ሆነው እንዲሰሩ ተደርጓል።

ተስፋዬ በወቅቱ ትክክለኛ ውሣኔ ባለመስጠቱ የተነሳ የሀገሪቱ ዜገች ድምፃችንን ተሰረቅን በማለት ተቃውሞ ሲያሰሙ በወያኔ አልሞ ተኩዋሽ ነፍሰ ገዳዮች በየመንገዱ ተገድለው እንዲጣሉ ያስደረገ ጨካኝ እና ወንጀለኛ መሆኑ እየታወቀ መልሶ አሁን የምርጫ ቦርድ ዋና ፀኃፊነት ቦታ መስጠታቸው አሁንም በለመደው መንገድ ሽምጥጦ እየዋሸ የወያኔን እድሜ እንዲያራዝም ታስቦ ነው ሲሉ የመመረጡን ዜና የሰሙ በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በብስጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ራሄል እና ኤርሚያስ የተባሉት ሁለት የወያኔ ግልግል ካድሬዎችም ለወራት በተስፋዬ መንገሻ ስር ሆነው ስራውን እንዲያጠኑ ከተደረጉ በኋላ ሁለቱም በምክትል ፀኃፊነት እንዲሰሩ መመደባቸውም ታውቋል።

ዛሬ የሀገሪቱ ሕዝቦች በኑሮ ወድነት የተነሳ በሐሳብ ውስጥ ተዘፍቀው ባለበት፣ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በመላ ሀገሪቱ ባልተጠናቀቀበትና አሓዙ ባልተገለፀበት በዚህ ወቅት ወያኔ የምርጫ ዘመቻ ለማድረግ ውስጥ ውስጡን እየተሯሯጠ መገኘቱ ቀደሞም ለሕዝብና ለሀገር ቅንጣት ታህል ቁም ነገር የሌለው ለራሱ ብቻ የሚኖር ሀገር በታኝና ሕዝብን ገዳይ የታጐረበት ቡድን ነው ሲሉ አንድ አዛውንት በእልህና በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

የወያኔው መሠሪ ቡድን ወደፊት በስልጣን ላይ ለመቀጠል የይስሙላ ምርጫ ለማድረግ እየተሯሯጠ ባለበት ወቅት በችግር ምክንያት አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ከተማ እየተሰደዱ በልመና ስራ ላይ የተሰማሩትን ዜጐች እያፈሰ ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ እያጐራቸው በቀን ቁራሽ ዳቦ እየሰጠ መልሶ ለእስር የዳረጋቸው ሲሆን፣ በአንፃሩ «ልመና ቻው» በሚል ስያሜ ለእነዚህ ዜጐች መርጃ የሚሆን ገንዘብ ለማሰባሰብ የመዚቃ ኮንሰርት ተዘጋጅቶ የነበረ መሆኑን የዝግጅቱ ታዳሚዎች ገልፀው እሁድ ታህሳስ 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገው የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ የተገኘ ቢሆንም የወያኔ ቡድን በስማቸው ለተነገደው ሳይሰጥ ዙሪያውን በችግር ለተወጠረበት ወታደራዊ ውጥረት መርጃ ያደረገው መሆኑንም ሁኔታውን በቅርበት የሚያውቁት ወገኖች ገልፀዋል።

ቀድሞም ወያኔ በዘረጋው እርስ በእርስ በአይነ ቁራኛ መጠባበቅ እና የማፈናቀል ስራ አካባቢያቸውንና የትውልድ ቀያቸውን ለቀው ወደ ከተማ የተሰደዱ ዜጐችን በአግባቡ ሥራ ፈጥሮ ማሰራት ሲችል የወያኔ ቡድን እራሱ በፈጠረው ችግር ምክንያት ተሰደው ከተማ የገቡትን ዜጐች «ከተማ ያቆሸሻሉ» በሚል እያፈሰ በካምፕ ውስጥ

አጉሯቸው መገኘቱ አሳዛኝና ህዝብ በድህንቱ በሀገሪቱ ውስጥ የመኖር መብቱ የተገፈፈ መሆኑን ያሳያል ሲሉ በርካታ ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች በብስጭትና በሀዘን ሲገልፁ ተስተውሏል፡፡

የወያኔ ቡድን በውስጥም በውጭም ተወጥሮ መረጋጋት በተሳነው በዚህ ወቅት በሀገሪቱ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የዘረፋ ተግባር ተስፋፍቶ መገኘቱ ተሰማ፡፡

ሕዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ከአዲስ አባ ወደ ደሴ ከተማ በመንዝ ላይ ያሉትን 27 አይሱዙ የጭነት መኪና ሹፌሮች ገንዘብና ወርቅ የተዘረፉ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ለቁልቢ ገብርኤል በዓል ለማክበር ወደ ሐረር በ5 አውቶቡስ ተሳፍረው ሲጓዙ የነበሩትን ምዕመናን አስቁመው ገንዘብ፣ ልብስና ወርቅ የተዘረፉ መሆኑን የዘረፋው ሰለባ ከሆኑት ውስጥ አንደኛው ገልፀዋል፡፡

በቀን ከ11 ሰዓት በኋላ በየትኛውም የሐገሪቱ አቅጣጫ መንቀሳቀስ ችግር እየሆነ የመጣው ጉዞ ታህሳስ 13 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ ወደ ቁልቢ ገብርኤል በመንዝ ላይ ሳሉ አድፍጠው የሚጠባበቁት ታጣቂ ኃይሎች በአምስት አውቶቢሶች ሲጓዙ የነበሩትን ምዕመናኖች አስቁመው ዝርፊያ የፈፀሙባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

በጅማ፣ በጐንደር፣ በደሴና በሐረር መስመሮች የተጀመረው ዘረፋ ወደፊት በቀን በጠራራ ፀሐይ በአዲስ አበባ ሊከሰት እንደሚችል የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ስጋታቸውን ገልፀው አሁን እየታየ ያለው ወያኔ ሐገሪቱን ለማስተዳደር ከአቅሙ በላይ እንደሆነና አፅሙ ብቻ ተገትሮ የቀረ መሆኑን የተረዳንበት ወቅት ላይ ነው ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ይገልፃሉ፡፡

ለወራት ያህል በሻዕቢያና በወያኔ በኩል ሲታሽና ሲወጠር የነበረው የጦርነት ዝግጅት ታህሳስ 16 ቀን ረፋዱ ላይ በፆረና ግንባር መጀመሩን የሻዕቢያ ቴሌቭዥን ይፋ ማድረጉ ታወቀ፡፡

ሻዕቢያና ወያኔ አቅማቸው ከሚፈቅደው በላይ ሕዝባቸውን ለረሀብ፣ ሀገራቸውን ለድህነት ዳርገው ሁለቱም ቡድኖች ባሉበት ስልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ብቻ አንደኛው አንደኛውን ለመጣል ከፍተኛ የጦርነት ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተው ረቡዕ ታህሳስ 16 ቀን 2000 ዓ.ም መጀመሩን የሻዕቢያ ቴሌቭዥን ገልጿል፡፡

የጦርነቱ መጀመር አይቀሬ እንደነበር በርካታ ምሁራኖች ጭምር ሥጋታቸውን ሲገልፁ የነበረ ሲሆን እንደተጠበቀውና እንደተገመተው ማንም ይቅደም ማን ግን ጦርነቱ መጀመሩ የታወቀ ሲሆን ከዚህ ቀደም እጅግ ብዙ ሺህ ኢትዮጰያውያንን የበላው ውጊያ አሁንም መቀስቀሱ አይቀሬ መሆኑን ቀድሞም ስጋታቸውን ሲገልፁ የነበሩት በርካቶች ናቸው፡፡

የወያኔ ቡድን እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በማለት እድሜውን ለማዝረም የተገኘውን እርምጃ ሁሉ ከመውሰድ ወደ ኋላ የማይል ከመሆኑም ባሻገር የተባበሩት መንግስታት የድንበር አካላይ ኮሚሽን የወሰደውን ውሣኔ

አልቀበልም በማለቱ የተነሳ ዛሬ ለተነሳው ደም አፋሳሽ እልቂት መዳረጋችን የሚያሳዝን ነው ያሉት ምሁራኖቹ ቀደሞ ገና በ1992 ወደ ድርድር ሲገባ ጠንካራና አሳማኝ ማስረጃዎችን ይዞ መቅረብ እየተቻለ ከ80 ሺህ በላይ መስዕትነት የከፈሉበትን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባሉ ኢትዮጵያዊ ምሁራኖችን በጉዳዩ ላይ ከማሳተፍ ይልቅ እንደ ባዕድ በመቁጠር ወያኔና ጀሌዎቹ ብቻ በሚስጥር ዶልተው የማይረባና ተልካሻ ማስረጃ ይዘው ቀርበው ለሽንፈትና ለውርደት የደረጉን ሲሆን፣ ዛሬም ይህንን ጦርነት እንደገና ሌላ ስህተት ሰርተው በስህተት ላይ ሌላ ስህተት እየፈፀሙ ሀገሪቷን ለድህነት ሕዝቧን ለችጋር እያጋለጡ መሆኑ አሳዛኝ ነው ሲሉ በቁጭት እየገለፁ ይገኛሉ::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ «ፈፅሞ ጦርነት አናነሳም » እያለ በጀሌዎቹ በተወካዮቹ ምክር ቤት አባሎች ተብዬ ፊት ቀርቦ ሲደሰኩር እንዳልነበረ ዛሬ ውጊያ ተነስቶ የተፈራው ዕልቂት መጀመሩ ምንኛ አሳዛኝና አንጀት የሚያላውስ መሆኑን የገለፁት እነዚሁ ምሁራኖች ከዚህ ቀደም የመጀመሪያው ውጊያ ወቅት ተፈራ ዋልዋ መከላከያ ሚኒስትር በነበረበት ወቅት ለሁሉም ነገር ዝግጁ ነን ባለ ማግስት «የናቴ መቀነት አደናቀፈኝ» በማለት ሕዝቡን ሀገርህ ተወረረ አግዘኝ ማለቱን አስተውሰው አሁንም ተመሳሳይ ሁኔታ ሊከሰት የሚችል ቢሆንም ሕዝቡ የማይመለከተኝ ጦርነት ስለሆነ አልሳተፍም በማለት በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገለፅ አሁንም እንቀድሞው የሕዝብ ድጋፍ አገኛለሁ ብለው አስበው ከሆነ የወያኔ ሹማምንቶች የስህተት አረንቋ ውስጥ መዘፈቃቸውን አላወቁትም ማለት ይቻላል ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል::

የአሜሪካንን ተልዕኮ ለማስፈፀም ሲል ብቻ ሞቃዲሾ ጦሩን አዝምቶ በቀየኑ የሟች ወታደሮችን ስም ዝርዝር እየለቀመ ያለው ወያኔ በደረሰበት ከፍተኛ የሰውና የንብረት ኪሣራ በመቆጨት በየቀኑ ጦር እየላከ ቁጥራቸው ከ30-50 ሺህ የሚደርሱ ወታደሮችን አስገብቶ በጭንቀት ተወጥሮ ያለ ሲሆን አሁን ደግሞ በሰሜን በኩል እንዲህ ያለ ችግር ተከስቶበት የስንግ መያዙ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ላይ መድረሱን ያሳያል ሲሉም አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የወያኔ ቡድን ሁልጊዜ በውሸት ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ማድረጉን የዓለም መንግስታት ሁሉ የተረዱት ሲሆን ሰሞኑን በምስራቅ ኢትዮጵያ ከታጣቂዎች ጋር ውጊያ መክረሙን አለም አቀፍ ሚዲያዎች ሲገልፁ በአንፃሩ የወያኔ ቡድን በማስታወቂያ ሚኒስቴሩ በኩል ሐሰት ነው እያለ እራሱን እያታለለ እንዳልነበረ ታህሳስ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. ከኦብነግ ጋር ውጊያ ላይ መክረሙን አምኖ መግለጫ አወጣ::

የወያኔ መከላከያ ሚኒስትር አወጣው በተባለው በዙሁ መግለጫ ላይ ታህሳስ ወር መጀመሪያ ጀምሮ የኦብነግ ታጣቂ ኃይሎችን በማደን ላይ ተሰማርቶ እንደነበርና ሙሉ በሙሉ እንደደመመሰሰ የገለፀ ቢሆንም ሕዝቡ የወያኔን ዋሾነት

በግልፅ ጠንቅቆ ያወቀው በመሆኑ ዛሬስ ስንት የወያኔ ወታደር ተማርኮ ይሆን? እያሉ በመጠየቅ ላይ ይገኛሉ::

የወያኔ ቡድን ጦርነቱን በአሸናፊነት እየተወጣሁ ነው በማለት መግለጫ ያውጣ እንጂ በአሁን ሰዓት ዙሪያውን እንደብራና ተወጥሮ ያለበት ወቅት በመሆኑና ሕዝቡን ጉልበት አለኝ ብሎ ለማስፈራራት ያደረገው ጥረት ካልሆነ በስተቀር በዚሁ በምስራቅ በኩል በተደረገው ውጊያ ላይ ከፍተኛ ኪሣራ እንደደረሰበት የመከላከያ የዘመቻ መምሪያ ውስጥአዋቂ ምንጮቻችን አጋልጠዋል::

20ኛ ክፍለ ጦር ከዚህ ቀደም በዚሁ በኦጋዴን አካባቢ ለብዙ ጊዜ ሲዋጋ ቆይቶ ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶበት በርካታ ወታደሮች ሞተውበት በርካታ የጦር መሣሪያ ተማርከውበት በጦሩም ላይ የሞራል ድቀት ስለደረሰ 13ኛ ክፍለ ጦር ወደ ውጊያ እንዲገባ መደረጉን ምንጮቹ ገልፀው በኦጋዴን ክልል ውስጥ ሸላቦ፣ ገለልቻ እና በመሳሰሉት አካባቢዎች አሁንም በውጊያ ላይ ያሉ ሲሆን፣ በሕዳር 29 እና 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ወደ ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የዘመቱ ከደቡብ ኢትዮጵያ የመጡ መምህራን ከአራት ያላነሱ በተኩስ ልውውጥ መካከል መሞታቸው ሳይገለፅ የቀረ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው በትክክል ለዘመቻ መምሪያው የደረሰው ሪፖርት ያስረዳል ካሉ በኋላ በተደረገው ድንገተኛ ውጊያ በወያኔ ጦር ላይና በምስኪን መምህራኖች ላይ በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጐች እንደሞቱ መረዳት ተችሏል ሲሉ አብራርተዋል::

የወያኔ ቡድን መላው ሲጠፋበት ሰሞኑን ከኩባ ጋር አዲስ የወታደራዊ ስምምነት በምስጢር መፈራረሙን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

በኩባው ምክትል ፕሬዝዳንት መሪነት አንድ የልዑካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለ3 ቀናት የስራ ጉብኝት እንዲሁም በ1969 ዓ.ም በሱማልያ ወረራ ወቅት ለሞቱት ኩባውያን የሰማዕታት ሐውልት ተሰርቶ ለመመረቅ የመጡ መሆኑ ይገለፅ እንጂ ዋናው የኩባ ከፍተኛ ልዑክ የመጣበት አላማ ከወያኔ ባለሥልጣናት ጋር የወታደራዊ ስምምነት ለማድረግ እንደሆነ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ወያኔ የኩባ ወታደሮች የከፈሉበትን መስዋዕትነት ለማራከስ ከፍተኛ ቅስቀሳ ሲያደርግ የነበረ ቡድን መሆኑ እየታወቀ 17 ዓመታት ስልጣን ላይ ሲቆይ አንድ ቀን ሳያስታውስ ዛሬ ሀገሪቱ ዙሪያዋን ስትወጠር የኩባን የጦር መሪዎች በአማካሪነት ለማምጣት ሲባል ብቻ የኩባ ወታደሮች የሰማዕታት ሐውልት ምረቃ በሚል ሕዝቡን ለማታለል መሞከሩ ይደንቃል ሲሉም ምንጮቹ ያለውንና የነበረውን ሂደት በይፋ ገልፀዋል::

አክለውም በአንድ የሜጀር ጄኔራል ማዕረግ ባላቸው የኩባ ከፍተኛ መኮንን የተመራ የወታደራዊ ልዑካን ቡድን በምስራቅ በኦጋዴንና በሰሜን ግንባር ያሉትን ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች እንዲመለከቱ ተደርጐ በአሁን ሰዓት በመከላከያ ዘመቻ መምሪያ ውስጥ ቢሮ ተሰጥቷቸው እየሰሩ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

የቸገረው እርጉዝ ያገባል እንደተባለው የወያኔ በድን ኩባ የምታራምደውን ርዕዮተ ዓለም ሲያብጠለጥል እንዳልነበረ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ለግለሰብ ተሰጥቶት መናፈሻ ይሆናል የተባለውን ሐውልት በሱማልያ ወቅት ለተሰው ኩባ ወታደሮች የተሰራ ሐውልት ነው በማለት ሽፋን ሰጥቶ ሲጠላቸውና ሲያጣጥላቸው የነበሩትን ኩባውያን ድረሱልኝ እያለ መማፀኑ የወያኔን እስስትነት ባህርይ አጉልቶ የሚያሳይ ነው ሲሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ከሁለት ዓመት በፊት በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ከእነ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ጋር በሀገር ክህደት ወንጀል ወያኔ ከሏቸው የነበሩት ሁለት የሲቪክ ማህበረሰብ ተጠሪዎች የእስራት ቅጣት መወሰኑ ታወቀ::

አቶ ዳንኤል በቀለና አቶ ነፃነት ደምሴ የተመሰረተባቸው ክስ እያስከስሳቸውም በማለት ገና ከጅምሩ ነፃ እንዲወጡ የማስመሰል ድራማ ሲሰራ የነበረው የመሐል ዳኛ አዲል መሐመድ የተባለው የወያኔ ካድሬ በታህሳስ 16 ቀን 2000 ዓ.ምህረትም ውሣኔ ሲሰጥ በነፃ መለቀቅ አለባቸው በማለት የማስመሰያ ክርክር ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም በእለቱ በተሰጠው ውሣኔ ሁለቱም የሲቪክ ማህበራት ተጠሪዎት ልይ የሁለት ዓመት ከስድስት ወር እስራት እንደተፈረደባቸው ለማወቅ ተችሏል::

ከሁለት አመት ከሶስት ወር በፊት የተከፈተባቸው ይኸው የወንጀል ክስ ሲንከባለል ቆይቶ ታህሳስ 16 ቀን 2000 ዓም ውሣኔ ያገኙ ሲሆን የቅንጅት አመራሮች ይቅርታ ጠየቁ በተባለ ወቅትም እነዚሁ ሁለት የሲቪክ ማህበረሰብ ተጠሪዎች አንጠይቅም ብለዋል ተብሎ የተዘገበ ሲሆን፣ ማስረጃዎቻቸውን በማቅረብ ሲከራከሩ ቆይተው ምንም የሰሩት ወንጀል ባለመኖሩና የታሰሩት ብዙ በመሆኑ በነፃ መልቀቅ የወያኔን መንግስት ገመና የሚያጋልጥ በመሆኑ የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶ በአነስተኛ ቅጣት ማሳለፍ ግዴታ እንደሆነባቸው ለዳኞቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

በተደጋጋሚ ጊዜ ይሳደብ የነበረው የቀኝ ዳኛ ልዑል ገብረ ማርያም ባደረበት ሕመም የተነሳ በጦር ኃይሎች ሆስፒታል እየታከመ ሲሆን፣ ከሕመሙ ባለማገገሙ ምክንያት ሌላው የትግራይ ተወላጅ መኮንን ገብረ ሕይወት የተባለው ዳኛ ቦታውን ተክቶ እንዲሰራ መደረጉ ታውቋል::

የነበረውን የፍርድ ቤት ሒደትን በጥሞና ሲከታተሉ የነበሩት የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በእጅጉ በፍርድ አሰጣጡ ላይ ማዘናቸውን ገልፀው ከሀገር እንደወጡም ለማወቅ ተችሏል:: እነዚህ ሁለት የሲቪክ ማህበረሰብ ተጠሪዎች የተፈረደባቸው የእስራት ጊዜ ምንም እንኩዋን ሁለት ወራት ቢቀራቸውም በሀገሪቱ ሕግ ተደንግጐ እንደተቀመጠው ማረሚያ ቤት ውስጥ የገባ እስረኛ ሁለት ሶስተኛውን ጊዜ ከታሰረ አመክሮ ተሰጥቶት ሊለቀቅ እንደሚችል የሚገልፅ ሲሆን ፣በዚህም መሠረት ሁለቱ የሕሊና እስረኞች ውሣኔ በተሰጠ ማግስት በዚሁ ሕግ ተጠቅመው ከእስር ሊለቀቁ እንደሚገባ ገልፀው ምናልባትም ሰኞ ታህሳስ 21 ቀን

2000 ዓ.ም በዚሁ ሁኔታ ሊፈቱ ይችላሉ ተብሎ በቤተሰቦቻቸው አካባቢም በጉጉት እየተጠበቁ ነው::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ነፍስ አባት ናቸው የተባሉት የፖለቲካ ተሿሚው አባ ገብረ መድህን አሜሪካ ሰራሽ መኪና ለመሸለም ዝግጅት መጀመሩን የቤተክህነት ምንጮቻችን ገለፁ::

ዘመናዊና እጅግ ዋጋው ውድ እንደሆነ የሚታወቀውን ሐመር መኪና ለአባ ገብረ መድህን ለመሸለም የራሴ ናቸው ያሏቸውን ሰዎች በአስተባባሪ ኮሚቴነት መርጠው ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ከየቤተክርስቲያኑ ሕዝብ የሚሰጠውን ገንዘብ ሙዳይ ምፅዋቱን ገልብጠው ለአለማዊው አባት መኪና ሊገዙ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል::

ከ6 ማሊዮን ብር በላይ እንደሚፈጅ የሚታወቀው ይኸው አሜሪካ ሰራሽ ሐመር የተባለውን መኪና በራሳቸው በአባ ገብረመድን ፍላጐትና ትዕዛዝ ኮሚቴ አቋቁመው ከየአድባራቱ ገንዘብ እንዲሰበሰብ ካደረጉ በኋላ መልሰው «የሚሊኒየሙ አባት» በሚል ለመሸለም እራሳቸውን ያዘጋጁ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች አንድም ቀን ለመንፈሳዊ እምነታቸው ሳይጨነቁ አልፎ ተርፎ በፖለቲካ ውስጥ እጃቸው ተነክሮ ባለበት በዚህ ወቅት የሚሊኒየሙ አባት ተብሎ ለመሸለም ሲዳክሩ መታየታቸው አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ሲሉ እነዚሁ ምንጮች ገልፀዋል::

በአሁኑ ሰዓትም ከመሪው ከመለስ ዜናዊ እኩል ጥይት የማይበሳው መኪና የሚንጓዙበት እንዳላቸው አባ ገብረመድህን የሀገሪቱ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀው እያሉ ምንም ያላሉት እኚሁ የአለማዊው ሰው ለራሳቸው የ6 ሚሊዮን ብር መኪና ተገዝቶ ይሰጠኝ ብለው ባዘዙት መሠረት ጥር 24 ቀን 2000 ዓ.ም በሚሊኒየም ፓርክ /የአላሙዲ መናፈሻ / ውስጥ የአሰጣጡ ስርዓት እንደሚከናወንም ምንጮቹ ሳይገልፁ አላለፉም::